## ለኢትዮጵያውያን መስማት የተሳናቸው ህፃናት የመደበኛ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ እየተከናወነ ስላለ ፕሮጀክት አጭር ገለጻ (በየኒንስ ተኽላይ)

ዲዲአይኤ ከአጋር ድርጅቱ ከዲዲፒ ጋር በመተባበር ለሶስት ዓመት የሚቆይ በመስማት የተሳናቸው አካቶ ትምህርት ዙርያ ለመስራት ተፈራርሞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ለፕሮጀክቱ መሳካት ከኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር ስራው እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ከ2009ዓ·ም· ጀምሮ ከ1-4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ የሥራዎቹን ክንውኖች በአጭሩ እንደሚከተለው አናቀርባለን፤

- በሁሉም የሃገሪቱ ክፍል የዳሰሳ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ስምንት ትምህርት ቤቶች ፕሮጀክቱን ለመተግበር ተመረጡ፡፡ አራቱ በአዲስ አበባ (አቃቂ፣ ቂርቆስ፣ ንፋስ ስልክና አራዳ) ክፍለ ከተሞች ሲሆኑ አራቱ ደግም አድዋ፣ በአዳማ፣ በመራዊና በሐዋሳ ከተሞች ይገኛሉ፡፡ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ አጎራባች ትምህርት ቤቶችን በማካተት ተጠቃሚነቱን በማስፋት ላይ ይገኛል፡፡
- ዲዲአይኤ ሁለት ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ፣ ስምንት ረዳት መምህራንና አንድ (1) የአይ.ቲ ባለሙያ እና አንድ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አወዳድሮ በመቅጠር ስራው በይፋ በሐምሌ 2008 ዓ.ም. ተጀምሯል፡፡ የተቀጠሩት ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

<u>የፕሮጀክቱ አላማ</u>

- በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች የመስማት የተሳናቸውን ትምህርት አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣
- ምቹ የሆነ የአካቶ ትምህርት ለመስማት የተሳናቸውና በከፊል መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ፣
- ለመስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከወላጆቻቸው፣ መምህራንና ትምህርት ማህበረሰብ የሚያጋጥማቸውን የተግባቦት ተግዳሮት ማቃለል፣
- ለመምህራንና መስማት የተሳናቸው ወላጆችን የምልክት ቋንቋ ስልጠና እና የመስማት የተሳናቸው ባህል በማስተማር ግንዛቤ ማስፋፋት፣ እስከ አሁን ድረስም ለ285 የሚሆኑት ተሰጥቷል፡፡

- በከፊል መስማት ለሚችሉ ተማሪዎች የጆሮ ምርምራ ማድረግና የጆሮ ማዳመጫ ድጋፍ ማድረግ፣
- ለመማር ማስተማሪያ የሚሆኑ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት ይገኙበታል፡፡
- የማስተማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣ እስካሁንም 12 ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች፣ 8 ኤልሲዲ ፕሮጀክተሮች፣ ደብተር፣ እርሳስ፣ እስክርቢቶ ለ8ቱም ትምህርት ቤቶች ተሰራጭተዋል፡፡

እንቅስቃሴዎቹን በተመለከተ ምስላዊ ገለጻ በውስጥ ገጽ ይመልከቱ፡፡